መልእክት ሁለት

**እግዚአብሔር፣ ሰው እና ሰይጣን**

የመጽሐፍ ቅዱስ ንባብ ክፍል፦ ኢዮ. 1፥6-12፤ 2፥1-7፤
ማቴ. 12፥26፤ ዕብ. 2፥14፤ ሮሜ 16፥20፤ ራእ. 12፥5፣ 7-11

**I. መላው መጽሐፍ ቅዱስ የእግዚአብሔርን፣ የሰውን እና የሰይጣንን ነገሮች የሚመለከት ዘገባ ነው፤ ስለዚህ፣ መጽሐፍ ቅዱስን በማንበባችን ውስጥ የእግዚአብሔርን እና የሰውን ነገሮች የሚመለከተውን ብቻ ሳይሆን የሰይጣንን ነገሮች የሚመለከተውንም ጭምር ማወቅ ያስፈልገናል—ዘፍ. 1፥1፣ 26-28፤ 3፥1፣ 4፣ 15፤ ኢሳ. 14፥12-14፤ ሕዝ. 28፥12-19፦**

ሀ. ሰይጣን እግዚአብሔር ምድርን ከመፍጠሩ በፊት በእግዚአብሔር የተፈጠረ መልአክ እና የተቀባ ኪሩብ ነበር፤ ከመላእክት መካከል ከፍ ያለው ነበር—ቁ. 12-15፤ ኢዮ. 38፥4-7፦

1. ሰይጣን “የንጋት ልጅ አጥቢያ ኮከብ” (ኢሳ. 14፥12)፣ ከመጀመሪያዎቹ መላእክት አንዱ የሆነ በአጽናፍ-ዓለም “ንጋት” ጊዜ በእግዚአብሔር የተፈጠረ፣ የመላእክት ሁሉ አለቃ ለመሆን በእግዚአብሔር የተሾመ ነበር (ሕዝ. 28፥14፤ ይሁ. 9)።
2. የተቀባው ኪሩብ በቅድመ-አዳማዊው አጽናፍ-ዓለም ላይ ለመግዛት በእግዚአብሔር ተሹሞ ነበር (ሉቃ. 4፥6)፤ የተቀባው ኪሩብ ለእግዚአብሔር እጅግ የቀረበ ነበር፣ ንግሥና እና ክህንነት ያለው በመሆን በእግዚአብሔር ፍጥረት ውስጥ ከፍተኛውን ስፍራ ይዟል (ሕዝ. 28፥13)።

ለ. የሰይጣን በእግዚአብሔር ላይ ማመጽ በኢሳይያስ 14፥13-14 እና በሕዝቅኤል 28፥15-18 ተገልጧል፦

1. ሰይጣን በእግዚአብሔር ላይ ያመጸው በልቡ ውስጥ ከነበረው ትዕቢት የተነሣ ነው፤ ከውበቱ የተነሣ ልቡ ታበየ—ኢሳ. 14፥13-14፤ ሕዝ. 28፥17።
2. የሰይጣን ውጥን የእግዚአብሔርን ስልጣን ለመገልበጥ እና ከእግዚአብሔር ጋር እኩል ለመሆን ራሱን ከፍ ከፍ ለማድረግ ነበር፤ እግዚአብሔር ላይ በማመጹ፣ ሰይጣን ከእግዚአብሔር ጋር በተመሳሳይ ደረጃ ላይ መሆን ፈለገ—ኢሳ. 14፥13።

ሐ. ከአመጹ የተነሣ፣ ሰይጣን የእግዚአብሔር የውስጥ ጠላት፣ የእግዚአብሔር ጠላት ሆነ—ዘካ. 3፥1-2፤ ራእ. 12፥9፤ 20፥2፦

1. *ሰይጣን* “የውስጥ ጠላት” ማለት ነው፤ እንደ የእግዚአብሔር የውስጥ ጠላት፣ ሰይጣን እግዚአብሔርን ይቃወማል—ኢዮ. 1፥7፣ 12፤ 2፥1፣ 6፤ ራእ. 20፥2።
2. *ጠላት* የሚያመለክተው ከእግዚአብሔር መንግሥት ውጪ ያለውን ጠላት ሲሆን፣ *የውስጥ ጠላት* የሚያመለክተው ከእግዚአብሔር መንግሥት ውስጥ የሆነውን ነው።
3. ሰይጣን ከእግዚአብሔር መንግሥት ውጪ ያለ የእግዚአብሔር ጠላት ብቻ ሳይሆን በእግዚአብሔር ላይ የሚያምጽ ከእግዚአብሔር መንግሥት ውስጥ የሆነ የእግዚአብሔር የውስጥ ጠላትም ጭምር ነው።

**II. በመጽሐፈ ኢዮብ 1 እና 2 ላይ ያለው ትዕይንት ኢዮብን በተመለከተ በሰማያት የተደረጉ ሁለት ምክክሮችን ይገልጣል—1፥6-12፤ 2፥1-7፦**

ሀ. ለኢዮብ ካለው የፍቅር ግድ መሰኘት የተነሣ፣ እግዚአብሔር ስለ ኢዮብ ለማውራት ሁለት ምክክሮችን አደረገ—1፥6፤ 2፥1።

ለ. “የአምላክ ልጆች፣” መላእክት በያሕዌ ፊት ለመቆም መጡ፣ የውስጥ ጠላት የሆነው ሰይጣንም ጭምር በመካከላቸው መጣ—1፥6፤ 2፥1፤ 38፥7፤ ተዛ. 1 ነገ. 22፥19-23፤ መዝ. 89፥5-8፦

1. በእግዚአብሔር ላይ ከአመጸ በኋላ፣ ሰይጣን በእግዚአብሔር ተኮነነ እንደውም ተፈረደበት—ኢሳ. 14፥12-15፤ ሕዝ. 28፥12-19።
2. የሰይጣን ወደ እግዚአብሔር መገኘት ውስጥ የመግባት መብት ገና አልተወሰደበትም ነበር—ተዛ. ራእ. 12፥10።

ሐ. በጥበቡ እና በሉአላዊነቱ እግዚአብሔር ፍርዱን በሰይጣን ላይ አልፈጸመበትም ነበር ነገር ግን በኢኮኖሚው መፈጸም ውስጥ ያለን የሆነ አሉታዊ ፍላጎትን ለማሟላት አንዳች ነገር እንዲያደርግ የተወሰነ የጊዜ ገደብ ሰጠው፦

1. እግዚአብሔር ኢዮብ በእግዚአብሔር የተሞላ ይሆን ዘንድ ያለውን ነገር ሁሉ ለመግፈፍ ኢዮብን ለመጉዳት የሚያስፈልገውን ነገር እንዲያደርጉ ከላቁት መላእክቱ መካከል ማናቸውንም መጠየቅ አይችልም አይጠይቅምም—ኢዮ. 1፥1፣ 8፣ 11-12፤ 2፥3-7።
2. ሰይጣን ኢዮብ ያሉትን ነገሮች እና በሥነ-ምግባር የደረሰበትን ደረጃ መግፈፍ የሆነውን የእግዚአብሔርን ውጥን መፈጸም የሚችል እና የሚፈጽመው በአጽናፍ-ዓለም ልዩና-ብቸኛው ማንነት ነበር—ቁ. 3።

3. በምዕራፍ 1 እና 2 ያለው ትዕይንት እግዚአብሔርን በሚወዱት ላይ የሚያደርገውን የእግዚአብሔርን የከፋ ማደብ ለማስፈጸም ሰይጣን እንደ አስቀያሚ መሣሪያ በእግዚአብሔር ጥቅም ላይ ለመዋል ሆን ተብሎ ነጻ ሆኖ እንደሚቆይ ያሳየናል—ተዛ. ሉቃ. 22፡31-32።

**III. ሰይጣን የራሱ መንግሥት የጨለማው ስልጣን አለው—ማቴ. 12፡26፤ ሐዋ. 26፡18፤ ቆላ. 1፡13፦**

ሀ. ሰይጣን የራሱ ስልጣን (ሐዋ. 26፡18) እና እንደ ገዢዎች፣ ስልጣናት እና የዚህ ዓለም የጨለማ ዓለም-ገዢዎች የእርሱ የበታች አካላት የሆኑ የራሱ መላእክት (ማቴ. 25፡41) አሉት፤ በመሆኑም፣ የራሱ መንግሥት፣ የጨለማው መንግሥት አለው (ቆላ. 1፡13)።

ለ. ሰይጣን የዚህ ዓለም ገዢ እና በአየር ላይ ስልጣን ያለው አለቃ ነው—ዮሐ. 12፡31፤ ኤፌ. 2፡2፦

1. *በአየር ላይ ስልጣን ያለው* ከሚለው አቻ ማብራሪያ ጋር የተቀመጠው *መንፈስ* (ቁ. 2) የሚያመለክተው ሰይጣን ገዢ የሆነበትን የኃይል ጥቅል-ድምር፣ የክፉ መላእክት ስልጣናት ሁሉ ጥቅል-ድምር ነው።

2. በኃጢአቶቻችን እና በበደሎቻችን ሙታን በነበርን ጊዜ (ቁ. 1)፣ "በዚህ ዓለም እንዳለው ኑሮ" (ቁ. 2)፣ በዓለም ዘመናዊ ገጽታ፣ የአሁኑ መንገድ፣ በሰይጣናዊው ስርዓት መሠረት ተመላለስን።

3. የጨለማው ገዢዎች፣ ስልጣናት እና የዓለም-ገዢዎች በእግዚአብሔር ላይ በነበረው አመጽ ሰይጣንን የተከተሉ እና በዓለም ባሉ አሕዛብ ላይ አሁን በሰማያት ሆነው የሚገዙ ያመጹ መላእክት ናቸው—ዳን. 10፡20።

4. ይህ የሚያመለክተው ዲያቢሎስ፣ ሰይጣን ከፍተኛውን ስፍራ የያዘበት እና ያመጹ መላእክት ከሥሩ የሆኑበት የራሱ መንግሥት እንዳለው ነው።

**IV. በምድር ላይ በነበረው አገልግሎት እና በመስቀል ላይ በነበረው ሞት፣ ጌታ ኢየሱስ በሰይጣን ላይ ድል ተቀዳጅቷል—1 ዮሐ. 3፡8፤ ማቴ. 27፡51-53፤ ቆላ. 2፡14-15፤ ዕብ. 2፡14፦**

ሀ. በምድር ላይ በነበረው አገልግሎቱ ድል-አድራጊው ክርስቶስ ዲያቢሎስን አሸንፎታል *ሥራዎቹንም* አፍርሷቸዋል (ደምስሷቸዋል)—ማቴ. 4፡1-11፤ 1 ዮሐ. 3፡8፦

1. ለመንግሥተ ሰማያት አገልግሎቱን ይፈጽም ዘንድ፣ ጌታ ኢየሱስ የእግዚአብሔርን ጠላት፣ ዲያቢሎስን፣ ሰይጣንን ማሸነፍ ነበረበት—ማቴ. 4፡1፣ 11።

   ሀ. ይህን እንደ ሰው ማድረግ ነበረበት፤ በመሆኑም የእግዚአብሔርን ጠላት ለመጋፈጥ እንደ ሰው ቆመ—ቁ. 6-7።

   ለ. የዲያቢሎስ የመጀመሪያውን ሰው፣ አዳምን መፈተኑ ስኬታማ ነበር፤ ሁለተኛውን ሰው፣ ክርስቶስን መፈተኑ ፍጹም ውድቀት ነበር—ቁ. 11።

2. በምድር ላይ በነበረው አገልግሎቱ ጌታ ኢየሱስ የዲያቢሎስን *ሥራ* አፈረሰ—1 ዮሐ. 3፡8፦

   ሀ. በ 1ኛ ዮሐንስ 3፡8 "እንዲያፈርስ" ተብሎ የተተረጎመው የግሪኩ ቃል "እንዳልነበረ እንዲያደርግ" ወይም "እንዲያጠፋ" ተብሎም ጭምር መተርጎም ይችላል።

   ለ. ስለዚህ የእግዚአብሔር ልጅ ተገለጠ፣ ይህም የዲያቢሎስን ኃጢአተኛ ተግባሮች እንዳልነበሩ ለማድረግ እና ለመደምሰስ፣ ማለትም፣ በሥጋ በሆነው በመስቀል ሞቱ በኩል በእርሱ፣ በክፉው የተነሣሣውን ኃጢአት ለመኮነን ነው፤ የኃጢአትን ኃይል፣ የዲያቢሎስን ኃጢአተኛ ባሕርይ ለመደምሰስ፤ ኃጢአትን እና ኃጢአቶችን ለማስወገድ—ሮሜ 8፡3፤ ዕብ. 2፡14፤ ዮሐ. 1፡29።

ለ. በመስቀሉ ድል-አድራጊው ክርስቶስ የዚህን ዓለም ገዢ ወደ ውጭ ጥሎታል፣ ዲያቢሎስን ደምስሶታል፣ አለቆች እና ስልጣናት እንዲገፈፉ አድርጓል፣ ሞትንም አጥፍቷል—12፡31፤ ማቴ. 27፡51፤ ዕብ. 2፡14፤ ቆላ. 2፡15፤ 2 ጢሞ. 1፡10፦

1. በመስቀል ላይ በነበረው *ሥራው*፣ ክርስቶስ የዚህን ዓለም ገዢ ወደ ውጭ ጥሎታል ዓለምንም ፈርዶበታል—ዮሐ. 12፡31፦

   ሀ. የዚህ ዓለም ገዢ ወደ ውጭ የተጣለው በሞቱ በነበረው የክርስቶስ *ሥራ* ሰይጣን ወደ ወጭ ሲጣል ነበር፤ በተመሳሳይ ጊዜ፣ ከሰይጣን ጋር የተገናኘው የዓለም ስርዓት ተፈርዶበታል—1 ዮሐ. 5፡19።

   ለ. የሰይጣን የአመጽ መሠረት ተናውጧል፣ የሰይጣን ምድራዊ መንግሥት ምሽጎችም ፈርሰዋል—ማቴ. 27፡51፦

2. በመሰቀሉ ክርስቶስ ዲያቢሎስን ሽሮታል (ደምስሶታል)—ዕብ. 2፡14፦

   ሀ. በቁጥር 14 "እንዲሽር" ተብሎ የተተረጎመው የግሪኩ ቃል "ምንም ወደ መሆን እንዲያመጣ፣ ምንም ውጤት የሌለው እንዲያደርግ፣ እንዲያስወግድ፣ እንዲደመስስ፣ ዋጋ-ቢስ እንዲያደርግ፣ እንዲያጠፋ ተብሎም ጭምር መተርጎም ይችላል።

   ለ. በስብዕናው እና በመስቀል *ሥራው* በኩል፣ ክርስቶስ ዲያቢሎስን ደምስሶታል—ዮሐ. 3፡14።

3. በመስቀል ላይ *ሥራው*፣ ክርስቶስ መልአካዊ ገዢዎችን እና ስልጣናትን እንዲገፈፉ፣ በገሃድ እንዲታዩ እና በእግዚአብሔር እንዲሸነፉ አድርጓል—ቆላ. 2፡15።
4. በመስቀል ላይ *ሥራው*፣ ክርስቶስ በዲያቢሎስ-ደምሳሽ ሞቱ (ዕብ. 2፡14) እና በሞት-ዋጪ ትንሣኤው (1 ቆሮ. 15፡52-54) በኩል ሞትን ምንም ውጤት የሌለው በማድረግ አጥፍቶታል—2 ጢሞ. 1፡10።

ሐ. በመንግሥቱ ወንጌል በኩል፣ እግዚአብሔር ሰዎችን በስልጣኑ የሚገዙ መንግሥቱ ይሆኑ ዘንድ ወደ ሰማያዊው ስልጣን አገዛዝ ሥር ያመጣቸዋል—ማቴ. 24፡14፤ ራእ. 1፡5-6።

## V. በክርስቶስ ኢየሱስ ውስጥ እንደሆኑ አማኞች እና የእግዚአብሔር ልጆች፣ በክርስቶስ በሰይጣን ላይ ድል-አድራጊዎች መሆንን መማር ያስፈልገናል—ኤፌ. 6፡12፤ 1 ጴጥ. 5፡8-9፤ 1 ዮሐ. 5፡18፦

ሀ. የሰይጣንን አሳብ (ሴራ) ቸል ማለት የለብንም—2 ቆሮ. 2፡11፦
1. "አሳብ" ተብሎ የተተረጎመው የግሪኩ ቃል "እቅዶች፣ ሴራዎች፣ ንድፎች፣ የተንኮል ስልቶች፣ ውጥኖች፣ አላማዎች" ማለት ነው።
2. ክፉው፣ ሰይጣን፣ በሁሉም ነገር ውስጥ ከሚታየው ነገር በስተጀርባ ነው እንዲሁም በሁሉም ነገር ውስጥ፣ በቤተ ክርስቲያን ሕይወት ውስጥም እንኳን ሳይቀር ይሠራል።

ለ. ከዲያቢሎስ ስልቶች በተጻራሪ መቆም እንችል ዘንድ የእግዚአብሔርን ዕቃ ጦር ሁሉ መልበስ ያስፈልገናል—ኤፌ. 6፡11፦
1. ዲያቢሎስ ክፉ ውጥኖች ብቻ ሳይሆን ውጥኖቹን ለማከናወን አታላይ ስልቶችም ጭምር አለው፤ እነዚህ ስልቶች ክፉ ሴራዎች ናቸው።
2. የእግዚአብሔርን ዕቃ ጦር ሁሉ መልበስ ከዲያቢሎስ ስልቶች በተጻራሪ ለመቆም ያስችሉናል—ቁ. 11።
3. በልዑሉ ቅዱሳን ላይ ከሆኑት የሰይጣን ስልቶች አንዱ ማዛል ነው (ዳን. 7፡21፣ 25)፤ ሰይጣን እያዛለን እንደሆነ በምናይ ጊዜ፣ የማዛል ዘዴዎቹን ለመቋቋም እና ለመቃወም ኃይል ይኖረናል።

ሐ. የሚውጠውን ፈልጎ እንደሚያገሣ አንበሳ የሚዞረውን የውስጥ ጠላት፣ ዲያቢሎስን ነቅተን ማየት ያስፈልገናል—1 ጴጥ. 5፡8፦
1. ነቅቶ ማየት በፊት ግንባር እንዳሉ ወታደሮች በጦርነት ውስጥ እንደሚደረገው ንቁ መሆን ነው።
2. በ 1ኛ ጴጥሮስ 5፡8 *ንቁ* የሚለው ቃል ውጊያን ያመለክታል፤ ጦርነት ውስጥ ገብተናል፣ ንቁ መሆንም ያስፈልገናል።
3. ንቁ ከሆንን፣ በእምነታችን በመጽናት የውስጥ ጠላታችንን እንቃወመዋለን—ቁ. 9፦
   - ሀ. መቃወም መቋቋም ወይም መጋደል ሳይሆን በሚያገሣው ዲያቢሎስ ፊት በእምነታችን መሠረት ላይ እንደ ዓለት ጸንቶ መቆም ነው።
   - ለ. በ 1ኛ ጴጥሮስ 5፡9 ያለው *እምነታችሁ* የሚለው የሚያመለክተው የአማኞችን ውስጠ-ልምምዳዊ እምነትን፣ በእግዚአብሔር የመጠበቅ ኃይል እና የፍቅር ግድ መሰኘቱ ያላቸውን እምነታቸውን ነው።

መ. ሰይጣንን የምናሸንፍበት ምርጡ መንገድ በተዋሐደው መንፈሳችን መኖር ነው—1 ቆሮ. 6፡17፤ 1 ዮሐ. 5፡18፦
1. ሰይጣን ሊወርረው የማይችለው አንድ ስፍራ ብቻ አለ—መንፈሳችን—2 ጢሞ. 4፡22።
2. በሰይጣን ስልጣን ሥር መሆን አለመሆናችን በምናደርጋቸው ነገሮች አይወሰንም፤ ይልቁንም፣ በመንፈስ ወይም በሥጋ በመሆናችን ይወሰናል—ገላ. 5፡16-17።
3. በተዋሐደው መንፈስ ውስጥ እስከቆየን ድረስ፣ እንጠበቃለን፣ ሰይጣንም በእኛ ምንም መንገድ አያገኝም—1 ቆሮ. 6፡17፤ 1 ዮሐ. 5፡4-5፣ 18-21።

## VI. "የሰላምም አምላክ ሰይጣንን ከእግራችሁ በታች ፈጥኖ ይቀጠቅጠዋል"—ሮሜ 16፡20፦

ሀ. የሰይጣን መቀጥቀጥ ከቤተ ክርስቲያን ሕይወት—እግዚአብሔር ሰይጣንን ድል-ከሚነሣበት ጠንካራው መንገድ—ጋር ይገናኛል—ቁ. 20፣ 1፣ 16።

ለ. በሮሜ 16፡20 "ከእግራችሁ (ከእናንተ እግር)" ተብሎ የተተረጎመው የግሪኩ ቃል በብዙ ቁጥር ነው፤ ይህ አካሉን ያመለክታል—12፡5፦
1. ሮሜ 16 አካሉን የሚያመለክተው አጽናፍ-ዓለማዊ በሆነ ትርጉም ሳይሆን የአካሉን አጥቢያዊ እና ተግባራዊ መገለጥ ነው።
2. ሰይጣንን ማስወገድ የአካሉ ጉዳይ እንጂ የግለሰብ ጉዳይ አይደለም።
3. ሰይጣን መቀጥቀጥ የሚችለው በአጥቢያ አብያተ ክርስቲያናት ባለው በአካሉ ተግባራዊ መገለጥ እግር ሥር ብቻ ነው—12፡5፤ 16፡1፣ 4፣ 16።

4. ሰይጣን ከእግራችን በታች የሚቀጠቀጠው እንደ የአካሉ ተግባራዊ መገለጥ ተገቢ የሆነ አጥቢያ ቤተ ክርስቲያን ሲኖረን ብቻ ነው—ቁ. 20።

ሐ. ሰይጣንን ከእግራችን በታች የሚቀጠቅጠው የሰላም አምላክ መሆኑ በትርጉም የተሞላ ነው—ቁ. 20፡-

1. የሰላም አምላክ የሚቀድሰው ነው፤ የእርሱ መቀደስ ሰላምን ያመጣል—1 ተሰ. 5፡23።
2. በእርሱ ሁለንተናችን ከውስጥ ሲቀደስ፣ ከእርሱ ጋር እና ከሰው ጋር በሁሉም መንገድ ሰላም አለን—ቁ. 13፤ ሮሜ 6፡19፣ 22፤ ዕብ. 13፡12።
3. ጸጥ ያልንና የተረጋጋን አድርጎ በማቆየት ደህንነቱ የተጠበቀ መሆኑን ለማረጋገጥ የሰላም አምላክ በክርስቶስ በልባችን እና በአስተሳሰቦቻችን ዙሪያ ስለሚቃኝ የእግዚአብሔር ሰላም ልባችንን እና አስተሳሰቦቻችንን ይጠብቃል፣ ነቅቶ ይመለከታል—ፊልጵ. 4፡7።

**VII. *ወንዱ-ልጅ ወደ እግዚአብሔር ዙፋን ከተነጠቀ በኋላ፣ በሰማይ ውጊያ አለ፣ ሰይጣን እና መላእክቱ ወደ ምድር ተጥለዋል፣ የእግዚአብሔርም መንግሥት ተገልጧል—ራእ. 12፡5፣ 7-11፡-***

ሀ. ወንዱ-ልጅ በቤተ ክርስቲያን ቦታ የሚቆሙትን፣ መላዋ ቤተ ክርስቲያን ልትወስደው የሚገባውን ስፍራ የሚወስዱትን እና የቤተ ክርስቲያንን ሥራ የሚሠሩትን ድል-ነሺዎቹን አካቶ ይዟል—2፡7፣ 11፤ 12፡5፡-

1. ወንዱ-ልጅ ያለማቋረጥ በምድር ላይ የእግዚአብሔርን ጠላት፣ ሰይጣንን በመዋጋት ሁል ጊዜ የተጠመደ ነው።
2. ሰይጣንን ከሰማይ ወደ ውጭ ለመጣል ጦርነት ይካሄድ ዘንድ ወንዱ-ልጅ፣ ድል-ነሺዎቹ፣ እንዲደርሱ ሰማይ እየጠበቀ ነው፡-

   ሀ. በድል-ነሺ አማኞች በሰይጣን ላይ የሚካሄደው ጦርነት በእውነቱ የጌታ ፍርድ በእርሱ ላይ መፈጸሙ ነው—ዮሐ. 12፡31።

   ለ. በመጨረሻ፣ በመዋጋታቸው በኩል፣ ሰይጣን ከሰማይ ወደ ውጭ ይጣላል—ራእ. 12፡8-9።

ለ. አሁን ዲያቢሎስ፣ ከሳሹ፣ አማኞችን ቀንና ሌሊት በእግዚአብሔር ፊት እየከሰሰ ነው፣ ነገር ግን ወንዱን-ልጅ የሚያዋቅሩት እና በእግዚአብሔር ጠላት፣ በሰይጣን ተቃውሞ የደረሰባቸውና የተሰደቡት ድል-ነሺ አማኞች ድል-ይነሡታል—ቁ. 10-11፡-

1. "ከበጉ ደም የተነሣ" ድል-ይነሡታል—ቁ. 11፡-

   ሀ. ለቤዛነታችን የሆነው የበጉ ደም ዲያቢሎስ በእኛ ላይ ላለው ክስ ሁሉ መልስ ይሰጣል በእርሱም ላይ ድል-ይሰጠናል።

   ለ. የዲያቢሎስ ክስ በተሰማን ጊዜ ሁሉ ይህን ደም መተግበር ያስፈልገናል—ሮሜ 3፡25፤ 1 ዮሐ. 1፡7።

2. "ከምስክራቸውም ቃል የተነሣ" ድል ይነሡታል—ራእ. 12፡11፡-

   ሀ. የምስክራቸው ቃል ዲያቢሎስ በጌታ መፈረዱን የሚመሰክር ነው—ዮሐ. 12፡31፤ ዕብ. 2፡14።

   ለ. የዲያቢሎስ ክስ በተሰማን ጊዜ ሁሉ፣ ጌታ በእርሱ ላይ የፈጸመውን ድል በሚገልጡ ቃላት ማወጅ አለብን።

3. ድል-ነሺዎቹ የነፍስ-ሕይወታቸውን አይወዱም—ራእ. 12፡11፡-

   ሀ. የነፍስ-ሕይወታችንን አለመውደድ ሰይጣንን ድል-ለመንሣት፣ ሰይጣንን ለማሸነፋችን መሠረቱ ነው።

   ለ. የነፍስ-ሕይወታችንን አለመውደድ ማለት የገዛ የነፍስ-ሕይወታችንን ለመተው ፈቃደኞች ነን እንዲሁም ለገዛ የነፍስ-ሕይወታችን ግድ-አንሰኝም ማለት ነው—ማር. 8፡34-35።

   ሐ. ሰይጣን አንድ የሰዎችን አይነት ብቻ ይፈራል—የገዛ የነፍስ-ሕይወታቸውን የማይወዱትን—ራእ. 12፡11።

ሐ. ወንዱ-ልጅ እጅግ አስፈላጊ ከሆነው ከእግዚአብሔር ዘመን ቀያሪ እንቅስቃሴ ጋር ይገናኛል—ማቴ. 6፡9-10፤ ራእ. 11፡15፤ 12፡10፡-

1. እግዚአብሔር ይህን ዘመን መፈጸም እና የመንግሥቱን ዘመን ማምጣት ይፈልጋል፣ ለዚህም እንደ ዘመን ቀያሪ መሣሪያው ወንዱን-ልጅ ማግኘት አለበት—ቁ. 5።
2. የወንዱ-ልጅ መነጠቅ ለቤተ ክርስቲያን ዘመን ፍጻሜን ያመጣል የመንግሥቱን ዘመንም ያስጀምራል—ቁ. 5፣ 10።
3. የወንዱ-ልጅ ወደ የእግዚአብሔር ዙፋን መነጠቅ፣ የሰይጣን ወደ ምድር መጣል እና በሰማይ ያለው አዋጅ የሚያመለክተው ወንዱ-ልጅ [የእግዚአብሔርን] መንግሥት ወደ ምድር እንደሚያመጣ ነው፤ ይህ ታላቁ የእግዚአብሔር ዘመን ቀያሪ እንቅስቃሴ ነው—ቁ. 5፣ 9-10፤ 11፡15።

*© 2020 Living Stream Ministry*